Amharisk

# ስለ ኦስሎ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል የተላላፊ በሽታዎች ሕክምና የተመላላሽ ክሊኒክ ወቅታዊ መረጃ

የኡለቮል የተላላፊ በሽታዎች ሕክምና የተመላላሽ ክሊኒኩ ከአርብ 13 ማርች ጀምሮ አገልግሎት የሚሰጠው ሙሉ በሙሉ በዲጂታል ነው። የተመላላሽ ክሊኒክ ሕንፃዎች ለመጪዎቹ ሳምንታት የሚዘጉ ሲሆን ፣ የዲጂታል የተመላላሽ ክሊኒኩ ግን ሙሉ በሙሉ ይሠራል። አሰራሩ እንደሚከተለው ነው:

ለምርመራ ወደ ተመላላሽ ክሊኒኩ መቅረብ የነበረባቸው የኤች አይ ቪ ታካሚዎች የደም ናሙና መስጠት እና የምርመራ ቀጠሯቸው ስለመሰረዙ መልእክት ይደርሳቸዋል። ያም ሆኖ ግን የቀጠሮ ቀኑ በሐኪሙ የቀጠሮ መጽሐፍ ውስጥ እንደሰፈረ ይቆያል ። ሐኪሙየታካሚውን ሰነድ ያነባል ፣ የበፊት የደም ናሙና ምርመራዎችን ያያል፣ የመጨረሻው የህክምና ቀጠሮ ላይ የተጻፈውን ማስታወሻዎች ያነባል፣ ኤሌክትሮኒካዊ የመድሃኒት ማዛዣ ይልካል፣ ማስታወሻዎሻ ይጽፋል እንዲሁም ለአዲስ የህክምና ክትትል በቀጠሮ ይጠራል። ሐኪሙ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለታካሚው ይደውላል። የህክምና ሰነዱን www.helsenorge.no ውስጥ ገብተው “pasientjournal” የሚለውን ከተጫኑ በኋላ የክልሎ የጤና ቢሮ የሆነውን Helse Sør-Øst for Oslo Universitetssykehus የሚለውን በመምረጥ ከፍተው ማንበብ ይችላሉ፧ ወይም ደግሞ minjournal.no ውስጥ ገብተው «journaldokumenter» ተጭነው በመክፈት ማየት ይችላሉ።

## በቅርቡ ኤች አይ ቪ እንዳለባቸው ተነግሯቸው ከኡለቮል ሆስፒታል ውጤቶችን እየተጠባበቁ ያሉ ሰዎች የምርመራ ውጤቶቹ እንደደረሱ ወዲያዉኑ የተለመደው ክትትል ይደረግላቸዋል ።

minjournal / helsenorge.no ውስጥ በሚከተለው መልኩ ከፍተው መግባት ይችላሉ:

በተመላላሽ ክሊኒኩ ውስጥ በየቀኑ ፀሐፊ ፣ ነርስ እና ሐኪም ይኖራሉ። አንዳንድ ታካሚዎችም በልዩ ቀጠሮ መምጣት ይችላሉ። እነዚህ ታካሚዎች በእግር በብስክሌት ወይም በግል መኪናቸው ቢመጡ በጣም ይመረጣል። ቢሆንም በኮሮና ቫይረስ የተያዙ በሽተኞች ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ሰው እንዲረዳው በተመላላሽ ክሊኒኩ ውስጥ የክፍል ኃላፊና ልዩ ሐኪም ቤንተ ማግኒ ይጠይቃሉ። የተመላላሽ ክሊኒኩ የኤች አይ ቪ ታካሚዎች በሙሉ ማለት ይቻላል በጥሩ ሁኔታ በሽታውን መቆጣጠር ስለሚችሉ የደም ናሙና ምርመራዎቹ ትንሽ መዘግየት የሚያሳሳብ ነገር አይደለም።

## ለኤች አይ ቪ መድኃኒቶች አዲስ የመድኃኒት ማዘዣን በተመለከተ

በየቀኑ ከሚወስዱት የኤች አይ ቪ መድሃኒትዎ ምን ያህል እንደቀሮት ይዩ። ሁለት ወይም ሶስት ወራት የሚያዘልቅ መድሃኒት ካሎት አዲስ የታዘዘን መድሀኒት የግድ በመጪዎቹ ጥቂት ሳምንታት ውስጥ ሂደው ማውጣት አያስፈልጎትም። Apotek1 i Storgata የመድኃኒት ቤት ማንኛውንም የኤችአይቪ መድኃኒቶች ማግኘት እና በአጭር ጊዜ ውስጥ የበለጠ ማዘዝ ይችላል።

በቅርቡ ወይም ደግሞ በመጭዎቹ አጭር ጊዜያቶች ውስጥ የሃኪም ቀጠሮ ካሎት፧ የመድኃኒት ማዘዣው ለቀጠሮ ሊቀርቡ ታስቦ በነበረው እለት ወዲያውኑ ይታደሳል። የመድኃኒት ማዘዣው ላይ ስህተት ካለ ወይም ለቀጠሮ ሊቀርቡ ታስቦ ከነበረው እለት በፊት

መድሃኒት ካስፈለጎት፣ ለኤች አይ ቪ ኖርዌይ (HivNorge) ይንገሩ እኛም መልእክቶን ለተላላፊ በሽታዎች ሕክምና የተመላላሽ ክሊኒኩ እናደርሳለን።

ሐኪምዎ የመድኃኒት ማዘዣውን ካደሰሎት www.helsenorge.no ከፍተው በመግባት «pasientjournal» የሚለውን ከተጫኑ በኋላ የክልሎ የጤና ቢሮ የሆነውን Helse Sør-Øst for Oslo Universitetssykehus የሚለውን በመምረጥ ስለ ማዘዣው ማንበብ ይችላሉ። እንዲሁም «Legemidler» የሚለውን በመጫን የመድኃኒት ማዘዣውን ማግኘት ይችላሉ ።

ኦስሎ ከሚገኘው ከ Apotek1 i Storgaten የመድኃኒት ቤት ጋር በመተባበር የመድኃኒት ማዘዣውን በዲጂታላዊ መልኩ ማግኘት ለሚቸግራቸው ሰዎች የሚረዳ መፍትሔም ተበጅቷል። የ Apotek1 i Storgata መድኃኒት ቤት መደበኛ ደንበኛ ካልሆኑ እና ከተቸገሩ የመድሃኒቶቹ ተጠቃሚ እንደሆኑ የሚያሳይ የመድኃኒት/ቶች ማኖርያ ሳጥን ወደ መድኃኒት ቤቱ ወስደው በማሳየት መድሃኒቶቹን ማግኘት ይችላሉ ። እንዲሁም የኡለቮል የተላላፊ በሽታዎች ሕክምና የተመላላሽ ክሊኒክ ታካሚ ሆነው ሳለ ነገር ግን መኖርያዎ ከኦሎሎ ውጭ ከሆነ እና ወደ ከተማ መምጣት ካልቻሉ መድኃኒት ቤቱን በስልክ በመደወል መድኃኒቶችን ማዘዝ ይችላሉ ። (ማንነቶን የሚያሳይ) መታወቂያ መያዝን አይርሱ።

ቤት መቆየትን ከመረጡ ወይም መገለል ካለቦት መድኃኒት ቤቱ መድኃኒቱን በፖስታ ሊልክሎት ይችላል። ይህን በተመለከተ ለበለጠ መረጃ መድኃኒት ቤቱ በቀጥታ ያነጋግሩ ።

እንዲሁም ይህ እንዴት እንደሚካሄድ መረዳት ከተሳኖ ኤች አይ ቪ ኖርዌይ (HivNorge) እንዲረዳዎ መጠየቅ ይችላሉ። ኤች አይ ቪ ኖርዌይ (HivNorge) በኢሜይል post@hivnorge.no ወይም በስልክ ቁጥር 21 31 45 80 ወይም 920 16 892 በመደወል ማግኘት ይቻላል።

## የመድኃኒት ማዘዣ ለሚያስፈልጋቸው የውጭ አገር ዜጎች

የኖርዌይ ሆስፒታል ታካሚ ያልሆኑ ግን ኦስሎን ለቀው መውጣት ያልቻሉ የኤችአይቪ መድሃኒት የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ወደ ኤች አይ ቪ ኖርዌይ (HivNorge) በስልክ 920 16 892 ከደውሉ መልእክታቸውን ለተላላፊ በሽታ የተመላላሽ ክሊኒክ እንዳርሳለን። ለኤች አይ ቪ ህክምናዎ የሚረዳ የመድኃኒት ማዘዣ እንዲያገኙ ክሊኒኩ ይተባበርዎታል።

## ኮሮና እና ኤች አይ ቪ

አንድ ሰው ኤች አይ ቪ ስላለው በኮሮና ቫይረስ የመያዝ አደጋ አላቸው ከሚባሉት ውስጥ ሊያካትተው ይችላል ወይ ወይም በቫይረሱ ቢያዝ በከባድ ደረጃ ሊታመም ይችላል ወይ የሚሉ በርካታ ጥያቄዎች ለኤች አ ይቪ ኖርዌይ (HivNorge) ይቀርባሉ። የኡለቮል ሆስፒታል የተላላፊ በሽታዎች ሕክምና ክፍል ሃላፊ የሚከተሉትን መልሶች ሰጥተውናል:

**እ.ኤ.አ. እስከ 17.03.2020 ድረስ ባለን መረጃ ኤች.አይ.ቪ የኮቪድ -19ን ቫይረስ ወደ ከባድ የበሽታ ደረጃ የማድረስ አደጋ አለው የሚል ድምዳሜ ላይ አልተደረሰም።**

**የኖርዌይ የጤና ዳይሬክቶሬቱ ማርች 23 ላይ ባወጣው የተሻሻለ መረጃ ደካማ የሆነ በሽታ የመከላከል አቅም ያላቸው ሰዎችን ለኮሮና በሽታ በተለየ መልኩ ከተጋለጡ ቡድኖች መካከል አካቷቸዋል። ይህ የዘለቀ የCD-4 ህዋሳቶች ቁጥር ማነስ ያላቸው የኤች አይ ቪ ተሸካሚዎች መካከል አብዛኞቹን ያካትታል።**

ሌሎቹ የሚያሰጋቸው ቡድኖች የዕድሜ መግፋት፣ ውስጥ ለውስጥ ስር የሰደዱ እንደ የልብና የደም ቧንቧ በሽታ ፣ የስኳር በሽታ ፣ ስር ሰደድ የሳንባ በሽታ ፣ ካንሰር ፣ ከፍተኛ የደም ግፊት ፣ ከመጠን ያለፈ ውፍረት ያለባቸው እና ሲጋራ አጫሾች ሲሆኑ እነዚህ በኮሮና ቫይረስ ቢያዙ በከባድ የመታመም እድላቸው ከፍተኛ ነው።

የCD-4 ህዋሳቶች ቁጥር ማነስ እና ሌሎች ከባድ ህመሞች ካለቦት የመንግስት መስርያ ቤቶችን ምክሮች በደንብ መከተል በጣም አስፈላጊ ነው.

Amharisk

ከኖርዌይ የህዝብ ጤና ተቋም ለጥያቄዎ የሚሆን መልስ ማግኘት ካልቻሉ ኤች አ ይቪ ኖርዌይ (HivNorge)ን መጠየቅ ይችላሉ። ኤች አ ይቪ  ኖርዌይ (HivNorge) ከኡለቮል የተላላፊ በሽታ የተመላላሽ ክሊኒክ ጋር የቅርብ ግንኙነት ስላለው፣ ምናልባትም ህክምና ነክ የሆኑ ጥያቄዎች ካሎት የተላላፊ በሽታ ሃኪሞችን አነጋግረን መልሱን በተቻለን ፍጥነት እንሰጥዎታለን ።

የኖርዌይ የህዝብ ጤና ተቋም ለህብረተሰቡ የሚሰጠው አጠቃላይ ምክር እና በኖርዌይ ስላለው ሁኔታ ወቅታዊ መረጃን በተመለከተ እዚህ ላይ ማንበብ ይችላሉ ።